# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 26 ጥር 8 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## <<እስካልተጎነበስን ድረስ ማንም አይጋልበንም እንደሚባለው ሁሉም ለመብቱ ቀጥ ብሎ የሚቆም ከሆነ ምርጫውን በትክክል ማስፈፀም እና ልእልናችንን ማረጋገጥ እንችላለን።

>> አንዷለም አራጌ የኢዜማ ም/መሪ



# < <እስካልተነካበስን ድረስ ማንም አይጋልበንም እንደሚባለው ሁሉም ለመብቱ ቀጥ ብሎ የሚቆም ከሆነ ምርጫውን በትክክል ማስፈፀም እና ልአልናችንን ማረጋገጥ እንችላለን፡፡> > አንዱለም አራጌ የኢዜማ ም/መሪ

ጥር 08 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ምርጫ ወረዳ 11 ጥር 03 ቀን 2012 ዓ.ም በስብሰባ ማእከል ከደጋፊዎቹ፣ አባላቱ እና የአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ሕዝባዊ ውይይት ማካሄዱ የሚታወስ ሲሆን በእለቱም የፓርቲው አመራሮች የሆኑት የፓርቲው ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ፣ የምርጫ ስትራቴጂ እና ማኔጅመንት ካውንስል አባል የሆኑት አማንይኹን ረዳ እና ምክትል መሪው አንዱለም አራጌ ከመድረክ የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስቶላቸው ምላሾቻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከቀረቡላቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ ምርጫው ለማጭበርበር የሚያስቡ ቡድኖች እንዴት አድርጋችሁ ነው የምትከላከሉት? ኢዜማ ወጣቶችን በሚመለከት ምን ስራ እየሰራ ነው? የኑሮ ውድነትን ለመቅረፍ ኢዜማ ምን ያስባል? ኢዜማ ለአካል ጉደተኞች ምን አይነት ፖሊሲ አለው? ኢዜማ ማሕበራዊ መሰረቱ ከተማ ብቻ ነው ይባላል ምን ትላላችሁ?

ምርጫው ለማጭበርበር የሚያስቡ ቡድኖች አሉ እንዴት ነው የምትከላከሏቸው? በሚል ለተነሳው ጥያቄ የፓርቲው ም/መሪ አንዱለም አራጌ ሲመልሱ ፓርቲያቸው ምርጫው ላይ ግብግብ እንደማይፈጥርና ለመብቱ የሚታገል፣ ሰብአዊ ልእልናውንና መብቱን የሚያስከብር ዜጋ እንዲፈጠር እንደሚሰራ ጠቁመዋል፡፡ ም/መሪው ምርጫ 1997ን እንደ አብነት በማንሳት በወቅቱ ለዴሞክራሲ መወለድ ከፍተኛ ትግል የተደረገው በፖለቲካ መሪዎች ሀይል እንዳልሆነ አስረድተዋል፡፡ ‹‹ያንን የመሰለ ድል የተገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲ በነበረው ፍላጎት እና ፍላጎቱን ለማሳካት ባደረገው ትግል ነው›› ብለዋል፡፡ ም/መሪው አያይዘውም ‹‹እስካልተነካበስን ድረስ ማንም አይጋልበንም እንደሚባለው ሁሉም ለመብቱ ቀጥ ብሎ የሚቆም ከሆነ ምርጫውን በትክክል ማስፈፀም እና ልእልናችንን ማረጋገጥ እንችላለን፡፡ ዜጎችን በማንቃትና በማስተማር እና ከዜጎችም በመማር ነው ኢዜማ ድምፁን ለመጠበቅ የሚሞክረው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ዜጋ ለድምፁ መከበር ዘብ መቆም አለበት፡፡ የመጨረሻውም ሆነ የመጀመሪያው መፍትሔ እሱ ነው›› ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ወጣቶችን በሚመለከት ኢዜማ ምን ስራ እየሰራ ነው? በሚል ለተነሳው ጥያቄም የምርጫ ስትራቴጂ እና ማኔጅመንት ካውንስል አባል የሆኑት አማንይኹን ረዳ ምላሽ ሲሰጡ ፓርቲያቸው የወጣቶችን ችግሮች በሚገባ ዳስሶ ችግሮቹ የሚቀረፉበትን የፖሊሲ አማራጭ እያዘጋጀ እንዳለ ጠቁመዋል፡፡ ፓርቲያቸው የወጣቶች ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን የወጣቶችን ችግር በፍፁም ቸል እንደማይለው ተናግረዋል፡፡ ‹‹ወጣቶች የነገ ሀገር ተረካቢ ብቻ ሳይሆኑ የዛሬ ሀገር ባለቤት መሆናቸውን ኢዜማ አፅንኦት ሰጥቶ የሚገነዘበው ጉዳይ ስለሆነ የወጣቶችን ችግር ለመቅረፍ እንሰራለን›› ብለዋል፡፡

የኑሮ ውድነትን ለመቅረፍ ኢዜማ ምን ይሰራል? በሚል ለተነሳው ጥያቄም አማንይኹን ረዳ ሰፊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ የኑሮ ውድነት የዜጎች ገቢ በቂ ካለመሆን ጋር የሚገናኝ ነው የሚሉት አማንይኹን፣ ይህንን ችግር ለመፍታት ኢዜማ አሸንፎ መንግሥት ቢሆን ዝቅተኛ የደሞዝ እርከን (Minimum Wage) እንዲኖር እንደሚያደርግ ጠቁመዋል፡፡ ፓርቲያቸው




የሠራተኛ ፖሊሲ እየቀረፀ እንዳለና በዚህ ፖሊሲ ውስጥ አንዱ የሚካተተው ሀሳብ ኢትዮጵያ ውስጥ በምን ያሕል ገንዘብ ነው አንድ ሰው መሰረታዊ የሚባሉ ፍላጎቶቹን አማልቶ መኖር የሚችለው የሚለው ሀሳብ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ በጥናት ተለይቶ ሁሉም መ/ቤት ከዛ የደሞዝ መጠን በታች ለሰራተኞቹ እንዳይከፍል እንደሚደረግም አስረድተዋል፡፡ ይህም የሚደረገው ዜጎች ካላቸው አነስተኛ ገቢ ምክንያት የሚኖረውን የኑሮ ውድነት ለመቋቋም መሆኑን ገልፀዋል ፡፡

ኑሮ የሚወደድበት ሌላኛው ምክንያት ገበያው ላይ በቂ ምርት ካለመኖር የተነሳ ነው የሚሉት አማንይኹን፣ ይህም ሊሆን ያልቻለው ግብርናው ባለማደጉ የተነሳ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ግብርናው ያላደገውም ዘርፉ በባለሙያ ባለመመራቱ የተነሳና ዘርፉ በቂ ገንዘብ እንዲያገኝ ባለመደረጉ የተነሳ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ኑሮ የሚወደድበት ሌላኛው ምክንያት የመንግሥት የመሬት ፖሊሲ አርሶአደሩ የመሬቱ ባለቤት ነኝ ብሎ መሬቱን በአግባቡ እንዲንከባከብ እድል ባለመስጠቱ የተነሳ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ግብርናው፣ ኢንደስትሪውና የአገልግሎት ዘርፉ እንዲያድግ በማድረግ በገበያው ውስጥ የምርት እጦት እንዳይኖር በቂ ትኩረት ሰጥቶ ፓርቲያቸው እየሰራ ስለሆነ ኢዜማ አሸንፎ መንግሥት ቢሆን አጠር ባለ ጊዜ ውስጥ የተረጋጋ ገበያ እንዲኖር በማድረግ ሕዝቡን ከኑሮ ውድነት ለማላቀቅ እንሰራለን ሲሉ ምላሻቸውን አጠቃለዋል፡፡

ለአካል ጉዳተኞች ኢዜማ ምን አይነት ፖሊሲ አለው በሚል ለተነሳው ጥያቄም ምላሽ የሰጡት አማንይኹን ረዳ፣ አካል ጉዳተኛ መሆን አለመቻል ነው ብሎ ፓርቲያቸው እንደማያስብና ፓርቲያቸው ኢዜማ ለአካል ጉዳተኞች ትኩረት በመስጠት የአካል ጉዳተኞች ፖሊሲ እየቀረፀ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ በዚህ የፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ውስጥ የሚሳተፉት የችግሩ ባለቤቶች የሆኑት አካል ጉዳተኞች መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ ፓርቲያቸው በቅርቡ ትልቅ ሀገራዊ ስብሰባ ከአካል ጉዳተኞች ጋር እንደሚያደርግና ለሁሉም አካል ጉዳተኞች በሚመች ቦታ ስብሰባውን የሚያደርግ መሆኑንም ገልፀዋል ፡፡

ኢዜማ ማሕበራዊ መሰረቱን የዘረጋው ከተሞች ላይ ብቻ ነው? በሚል ለተነሳው ጥያቄም በመድረኩ ላይ ያልነበሩት ከተሰብሳቢው ወገን በመሆን ሕዝባዊ ውይይቱን ሲከታተሉ የነበሩት የፓርቲው ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ዋሲሁን ተስፋዬ ምላሽ ሰጥተውበታል፡፡ ኢዜማ የት ቦታ ነው ያለው ሳይሆን የት ቦታ ነው የሌላችሁት ብለን ብንጠይቅ ለመመለስ ያመቻል ያሉት ኃላፊው ለምሳሌ ዛሬ (ጥር 03 ቀን 2012 ዓ.ም) ቤንሻንጉል ጉሙዝ ፓዊ ላይ ስብሰባ እየተካሄደ እንዳለ በተመሳሳይ ሰአት ሰቆጣ ላይ ስብሰባ እየተካሄደ በተጨማሪነትም አዳማ ላይም ስብሰባ እየተካሄደ እንዳለ ጠቁመዋል፡፡ በመላው ሀገሪቱ በሁሉም ቦታ ላይ አለን ያሉት ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ይህ ሁሉ የተሰራው ባለፉት ሰባት ወራት መሆኑንና ከ275 በላይ ቢሮዎች ተከፍተው ከ410 ምርጫ ወረዳዎች ላይ መዋቅር በመዘርጋት ፓርቲያቸው እየተንቀሳቀሰ እንዳለ አስረድተዋል፡፡ ‹‹ይህ ግን በቂ አይደለም›› ያሉት ኃላፊው ምርጫው የሚካሄደው በ547 ምርጫ ወረዳዎች ላይ ስለሆነ በቀበሌ፣ በቤትና በሰፈር ደረጃ አደረጃጀት በመዘርጋት ፓርቲያቸው መዋቅሩን እንደሚያሰፋ አስረድተዋል፡፡

# አድራሻ

**ስልክ**
+251118592950

**ኢሜይል**
ethzema@gmail.com

**ትዊተር**
www.twitter.com/ethzema

**ፌስቡክ**
www.facebook.com/ethzema

**የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)**

**ጥር 8 ቀን 2012 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**

# ኢዜማ በመርሳ ህዝባዊ ስብሰባ አካሄደ “የኢዜማ ቅድሚያ አላማ ሰላምን ማረጋገጥ ነው” ካውሰር እንድሪስ

ጥር 08 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የኢዜማ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ካውሰር እንድሪስ እና የኢዜማ የዞን አስተባበሪ በተገኙበት ህዝባዊ ስብሰባ አካሄደ፡፡

ህዝባዊ ውይይቱ ትኩረት ያደረገው መጪውን ምርጫ ዋና መወያያ በማድረግ ከኢዜማ የምርጫ ወረዳ አመራሮችና አባሎች ምን ይጠበቃል እና መሰል ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል፡፡ በከተማዋ ላይም የሚታየው ኮንትሮባንድ በዕለት ህይወታቸው ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረባቸው ለደኅንነታቸውም ስጋት እንደሆነ በተደጋጋሚ



ነዋሪዎቹ ገልጸዋል፡፡

በሀገራችን የሚፈጠሩ ብዙ ችግሮች እንዳሉ፤ በመርሳ አካባቢ ያለውን ሰላም ለማስጠበቅ እና ዘላቂታዊ ልማት እንዲኖር በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለውን፣ በመልካም ባህሪው የሚታወቅን፣ ለወደፊት በታማኝነት የሚያገለግልን መምረጥና ማስመረጥ እንዳለባቸው የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ካውሰር እንድሪስ በመግለጽ ሁሉም መብቱን እንዲያውቅ በደንብ መሰራት

# ኢዜማ በሰቆጣ ያካሄደውን ሕዝባዊ ስብሰባ ተከትሎ የአባልነት ጥያቄ የሚያቀርቡ ሰዎች በብዛት እየመጡ እንደሆነ ተገለጸ

ጥር 08 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በሰቆጣ ከተማ ያካሄደው ሕዝባዊ ስብሰባ በስኬት መጠናቀቅ ተከትሎ በወረዳው ነዋሪ የሆኑ በርካታ ሰዎች የአባልነት ፎርም ለመሙላትና አባል ለመሆን በተለያየ መንገድ ጥያቄ እያቀረቡ በብዛት እየመጡ ምዝገባ እያከናወኑ መሆኑን የኢዜማ የሰቆጣ ምርጫ ወረዳ ሊቀመንበርና የዞን አስተባባሪ የሆኑት አበበ ወልዴ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

በሦስት ምርጫ ወረዳ የተዋቀረው በስሩም 8 ወረዳዎችን በሚያስተዳድረው ሰቆጣ ህዝባዊ ስብሰባው ከተከናወነ በኃላ በህዝቡ ውስጥ ሰፍኖ የነበረው የፍርሃት ስሜት መወገዱን የተካሄደውን ስብሰባ ለመሳተፍ ከተለያዩ ቦታዎች ረጅም ርቀት በመጓዝ የመጡ እንደነበር በስብሰባውም ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ከመጠየቅ ባለፈ አስተያየት በመስጠት እንዲሁም በቁርጠኝነት በኢዜማ ውስጥ መሳተፍ እንደሚፈልጉ በስብሰባው ላይ በተነሳሽነት ፍላጎታቸውን ሲገልጹ እንደነበር አስተባባሪው ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ለኢዜማ አመራሮች ከታዳሚዎች ጥያቄዎች እንደቀረበላቸው ከቀረቡላቸውም መካከል ምርጫውን ኢዜማ ቢሸነፍ ይቀበላል ወይስ ሌላ የትግል ስልት ይከተላል? ለሚለው ኢዜማ በትክክለኛ ምርጫ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ከተሸነፈ ውጤቱን በፀጋ እንደሚቀበል በአመራሮቹ መገለጹን መዘገባችን ይታወቃል፡፡